የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት
የጸሀፊ (ክለርክ) ቢሮዎች አሰራሮች ማስታወቂያ
በኖቨምበር 2020 የተሻሻለ

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክኒያት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የጸሀፊ (ክለርክ) ቢሮዎች፣ በፍርድ ቤቱ በአካል የሚሰሩ ውስን ሰራተኞች በማድረግ ከርቀት (ሪሞት ስታተስ) መስራት ቀጥሏል። በቴሌፎን፣ ኢመይልና ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) በመጠቀም ለጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጁ ሰራተኞች አሉን። በጸሀፊ (ክለርክ) ቢሮዎች ስለሚከናወኑ ስራዎች በተመለከተ መረጃ ከታች ይገኛል።

ሰነዶችዎን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረግ የማይችሉ ከሆነ፣ በፖስታ በኩል መላክ ይችላሉ፣ ወይም በ500 Indiana Avenue, N.W በሚገኘው የሞልትርየ የፍርድ ቤት ህንጻ አንደኛ ፎቅ (ፈረስት ፍሎር) በሚገኘው የመረጃ ዳስ (ኢንፎርሜሽን ቡዝ) ቀጥሎ ባለው መጣያ ሳጥን (ድሮፕ ባክስ) ፋይል ስታምፕ አድርገው መጣል ይችላሉ።

አብዛኛዎቹ ችሎቶች (ሂሪንግስ) በተመደበው ዳኛ ከርቀት (ሪሞትሊ) ይካሄዳሉ። እባክዎን ሰነዶች ፋይል ሲያደርጉ የሁሉም አካላት የቴሌፎን ቁጥርና ኢመይል አድራሻ ያቅርቡ።

### ለአከራይና-ተከራይ የመከላከያ ትእዛዞች (ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ክፍያዎች

ተከራዮች ለአከራይና-ተከራይ የመከላከያ ትእዛዞች (ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) በጥሬ ገንዘብ መክፈል ይችላሉ። በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ክፍያዎች በማክሰኞና ሀሙስ ከ1፡00 ፒ.ኤም. እስከ 3፡00 ፒ.ኤም. በ500 Indiana Avenue, N.W በሚገኘው የሞልትርየ የፍርድ ቤት ህንጻ አንደኛ ፎቅ (ፈረስት ፍሎር) የመረጃ ዳስ (ኢንፎርሜሽን ቡዝ) ሊደረጉ ይችላሉ።

### ኤሌክትሮኒካዊ ክፍያዎች

ሱፒርየር ፍርድ ቤት ለተወሰኑ የፍርድ ቤት ክፍያዎች፣ ቅጣቶችና ወጪዎች፣ አዳዲስ የኤሌክትሮኒካዊ ክፍያ መግቢያዎቻችን (ፖርታልስ) በሆኑት ፐይፖርት (PayPort) እና ፕሮምፕትፐይ (PromptPay) በመጠቀም ክፍያዎች በመቀበል ይገኛል። ደቢት ካርድ፣ ክሬዲት ካርድ (አሜሪካን ኤክስፕረስ፣ ዲስካቨር፣ ማስተርካርድ፣ ቪዛ) ወይም ኤ.ሲ.ኤች. ኤሌክትሮኒካዊ ቼክ በመጠቀም ሊደረጉ ይችላሉ። ለያንዳንዱ ግብይት (ትራንዛክሽን) $1.00 የሚከፈል ሲሆን ደቢት ወይም ክሬዲት ካርድ መጠቀሚያ ተጨማሪ 2.5% ክፍያም ይከፍላሉ።

የሚከተሉትን ግብይቶች (ትራንዛክሽንስ) በአዲሱ ፕሮምፕትፐይ መግቢያችን (PromptPay portal) የሚከፍሉበት የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኝ (ኢንቮይስ) ይደርስዎታል፡

- የቦንድ (የገንዘብ ዋስ) ክፍያዎች (ለወንጀለኛና የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍያዎች በክሬዲትና ደቢት ካርዶች የሚደረጉ ክፍያዎች)፣
- የመከላከያ ትእዛዝ (ፕሮቴክቲቭ ኦርደር) ክፍያዎች፣
- ማእቀቦች (ሳንክሽንስ)፣
- ቅጣቶች፣
- የምዝገባና ኤስክሮ ክፍያዎች ጨምሮ ፍርድ ቤት ያዘዛቸው ክፍያዎች

ፐይፖርት (PayPort) በመጠቀም የሚከተሉት ክፍያዎች መክፈል ይቀጥላሉ፡

- የተረጋገጡ ቅጂዎች (ሰርቲፋይድ ካፒስ)፣
- የመዝገብ ፍለጋ ጥያቄዎች (ሬከርድ ሰርች ሪክዌስትስ)፣
- የጋብቻ ማመልከቻዎች፣ የጉዲፈቻ አቤቱታዎች፣ የማህተም መስበሪያ ማመልከቻዎች (አፕሊኬሽን ቱ ብሬክ ሲል)፣ የታተሙ የመዝገብ አይነቶች ሰነዶች ጥየቃ (ዳኩመንትስ ፎር ሲልድ ኬዝ ታይፕስ)፣
- የይግባኝ ማሳሰቢያዎችና ለቤት ውስጥ ብጥብጥ ጉዳዮች ፍርድ ቤት ያዘዛቸው ክፍያዎች፣ እና
- ለተወሰኑ የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ጉዳዮች ተጨማሪ ደብዳቤዎች (አዲሽናል ለተርስ) እና የፍርድ ቤት ወጪዎች

በዲሰምበር 2020፣ ሁሉም ኤሌክትሮኒካዊ ክፍያዎች በፕሮምፕትትፐይ (PromptPay) በኩል ብቻ ይደረጋሉ።

የኤሌክትሮኒካዊ ክፍያ መግቢያዎች (ፖርታልስ) ለመጠቀም ክፍሎቹን (ዲቪዥንስ) እንደሚከተለው ማግኘት ያስፈልጋል፡

| ክፍል (ዲቪዥን) | ቴሌፎን | ኢሜይል |
|---|---|---|
| የወንጀል ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን) | 202- 879-1840 | BondPayPortal@dcsc.gov |
| የፍትሐብሔር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)<br>- የፍትሐብሔር እርምጃዎች (ሲቪል ኤክሽንስ) ቅርንጫፍ<br>- የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ<br>- አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች (ስሞል ክለይምስ) ቅርንጫፍ | 202-879-1133<br>202-879-4879<br>202-879-1120 | CivilDocket@dcsc.gov<br>LandlordandTenantDocket@dcsc.gov<br>SmallClaimsDocket@dcsc.gov |
| የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) | 202-879-0157 | **ፍርድ ቤት ያዘዛቸው የሲ.ፒ.ኦ. ክፍያዎች**<br>FamilyCourtCIC@DCSC.gov<br><br>**ዲ.ቪ.ኤም. ቦንድና ፍርድ ቤት ያዘዛቸው ክፍያዎች**<br>BondPayPortal@dcsc.gov |
| የቤተሰብ ፍርድ ቤት | 202-879-1212 | **የመዝገብ (ኬዝ) ክፍያዎች**<br>FamilyCourtCIC@dcsc.gov<br>**ቅጂዎች**<br>FamilyCourtCertifiedCopies@dcsc.gov<br>**ጋብቻ**<br>MarriageBureauReceipts@dcsc.gov<br>**የዋስትና ክፍያዎች (ቦንድስ)**<br>FamilyBonds@dcsc.gov |
| የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) | 202-879-9460 | ProbateInquiries@dcsc.gov |
| የግብር ክፍል (ታክስ ዲቪዥን) | 202-879-1737 | TaxDocket@dcsc.gov |

ለሁሉም ሌሎች ክፍያዎች በhttps://www.dccourts.gov/superior-court/e-filing በሚገኘው የኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ ኢፋይሊንግ ሲስተማችን በመጠቀም ይክፈሉ።

የሰነድ መደበኛ ቅጂ ከፈለጉ ወይም ለሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች በጥሬ ገንዘብ መክፈል ከፈለጉ እባክዎን የክፍሉ (ዲቪዥን) ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) ዘንድ ይደውሉ።

እባክዎን ተደጋግመው ለሚጠየቁ ጥያቄዎች የዲ.ሲ. ፍርድ ቤቶች ድረገጽን ይጎብኙ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/Payment-Portal-FAQs.pdf።

**ቅጂዎችና የተረጋገጡ ቅጂዎች (ካፒስ ኤንድ ሰርቲፋይድ ካፒስ)**
ቅጂዎችና የተረጋገጡ ቅጂዎች (ካፒስ ኤንድ ሰርቲፋይድ ካፒስ) በሙሉ በሚመለከተው ክፍል (ዲቪዥን) ይሰጣሉ። እባክዎን፣ ሰነዶችን ከያንዳንዱ ክፍል (ዲቪዥን) እንዴት መጠየቅ እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት ከታች ያሉ መመርያዎች ይመልከቱ። የተረጋገጠ ቅጂን (ሰርቲፋይድ ካፒ) ኢ-ሜይል በመጠቀም ሲጠይቁ እባክዎን ርእሰ ጉዳይ (ሳብጀክት ላይን) በሚለው "Request for Certified Document "የተረጋገጠ ቅጂ ጥየቃ"" ብለው ይጻፉ። ለሁሉም የቅጂ ጥያቄዎች በሚላከው ኢ-ሜይል እየተጠየቀ ያለው ሰነድ ስም፣ የመዝገብ ቁጥር (ካለ)፣ በጉዳዩ ያሉ አካላት ሙሉ ስም፣ እና የእርስዎ ስም፣ ቴሌፎን ቁጥርና ኢ-ሜይል አድራሻ ያካትቱ።

**ሶስት ማህተሞች (ትሪፐል ሲልስ)**

የሶስት ማህተሞች (ትሪፐል ሲልስ) ጥያቄ በኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ ድረገጽ https://www.dccourts.gov/superior-court/e-filing በኩል መደረግ ይኖርበታል። ድረገጹ መጠቀም የማይችሉ ከሆነ እባክዎን የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ ኦፊስ) ዘንድ ይደውሉ።

**የኦዲተር ማስተር ቢሮ**

ሁሉም የኦዲተር ማስተር ችሎቶች ባሁኑ ጊዜ ዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት በመካሄድ ይገኛሉ። አካላት በአካል መቅረብ የለባቸውም። አካላት ችሎቱን በቴሌፎን ወይም በቪድዮ መሳተፍ ይኖርባቸዋል፣ እና ወደ ቢሮው በአካል ሪፖርት ማድረግ የለባቸውም። ችሎትን በርቀት እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ የሚያሳዩ መመሪያዎች ለሁሉም አካላት ይቀርባሉ።

አካላት ከኦገስት 1፣ 2020 ጀምሮ የወጡትን ሁሉንም ትእዛዞች ማክበር ይኖርባቸዋል። አስቀድመው ተቀጥረው የነበሩ ችሎቶችን ሌላ ቀነ ቀጠሮ የሚሰጡ፣ አዳዲስ ጉዳዮችን የችሎቶች ቀነ ቀጠሮ የሚሰጡ፣ እና ሰነዶች የሚቀርቡባቸው አዳዲስ ቀናት የያዙ የተለያዩ ትእዛዞችን ቢሮው እያወጣ ነው።

ሁሉም ሰራተኞች ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5፡00 ፒ.ኤም. ድረስ በርቀት ይገኛሉ። ሁሉም ሰነዶች በሰራተኞች በርቀት ሂደት እየተደረገባቸው ይገኛል። ሰነዶች በኢ-ሜይል ለAuditor.Master@dcsc.gov ወይም በፖስታ ለ፡ Office of the Auditor-Master, 500 Indiana Avenue NW, Washington, DC 20001 ማስረከብ ይችላሉ። ምስጢራዊ የሆኑ ሰነዶች ወደ AMFinancialBox@dcsc.gov በኢ-ሜይል መላክ ይችላሉ።

ሁሉም ችሎቶች የተደረጉባቸውና ሁሉም ሰነዶች የተረከቡባቸው ጉዳዮች በተመለከተ ሪፖርቶች በመዘጋጀት ይገኛሉ። ሪፖርቶች እንደተጠናቀቁ ለአካላት እንዲደርሱ ይደረጋል።

እባክዎን ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ቢሮውን በቴሌፎን ቁጥር 202-626-3280 ወይም በኢ-ሜይል በAuditor.Master@dcsc.gov ያግኙ።

**የፍትሐብሔር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)**

የፍትሐብሔር ክፍል በኢ-ፋይሊንግ (eFiling) በኩል የተላኩ ሰነዶች ሂደት ማድረጉ ይቀጥላል። አስቸኳይ አቤቱታዎች ለግምገማ ወደ ዳኛ ይላካሉ።

1. ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች፣ ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በhttps://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

2. ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች፣ ክፍያ አስቀድመው ላለመክፈል (የማመልከቻ ክፍያ ይተውልኝ) ማመልከቻን ማመልከቻውንና ሰነዶቹን ወደ Civilefilings@dcsc.gov በመላክ ፋይል

ማድረግ ይኖርባቸዋል። ክፍያ አስቀድመው ላለመክፈል (የማመልከቻ ክፍያ ይተውልኝ) ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ወይም ማመልከቻው የተከለከለ ከሆነ ከተከለከለ በኋላ ፋይል የሚደረጉ ሁሉንም ሰነዶች ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል መደረግ ይኖርባቸዋል።

a. የማመልከቻ ክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻዎች በድረገጻችን https://www.dccourts.gov/services/judge-in-chambers/in-forma-pauperis-fee-waiver ይገኛሉ።

3. የስም ለውጥ ማመልከቻዎችና፣ የሞት እና የልደት ምስክር ወረቀት ማሻሻያ ማመልከቻዎች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ (Case File Express) በመጠቀም፣ ፋይል የማድረጊያ ክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻ ጭምር ፋይል የተደረጉ ከሆነ ብቻ ደግሞ በኢሜይል ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

4. በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በመጠቀም ሰነዶችዎን ማስረከብ የማይችሉ ከሆነ ሰነዶችዎን ክፍያ ጨምረው በፖስታ በኩል ወደ: D.C. Superior Court, Civil Division, 500 Indiana Avenue, N.W., Washington, D.C. 20001 በመላክ፣ ወይም ሰነዶችዎንና ክፍያውን በሞልትሪ ፍርድ ቤት ህንጻ ባለው መጣያ ሳጥን (ድራፕ ባክስ) በመክተት ማስረከብ ይችላሉ።

5. የአከራይና ተከራይ ወይም የመኖሪያ ቤት ሁኔታዎች ጉዳይ ያለዎት ከሆነና ሰነዶች ወይም የክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ፣ ድጋፍ ለማግኘት የአከራይና ተከራይ የህግ ድጋፍ መረብን (ላንድሎርድ ቴናንት ሊጋል አሲስታንስ ኔትዎርክ) በ202-780-2575 ማግኘት ይችላሉ።

6. የነይበርሁድ ሊጋል ሰርቪስስ ፕሮግራም የተባለው የህግ አገልግሎቶች የሚሰጥ ፕሮግራም አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ጉዳዮች የህግ መረጃ ያቀርባል። በኤን.ኤል.ኤስ.ፒ. አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ሀብት ማእከል (ስሞል ክለይምስ ሪሶርስ ሰንተር) የ24-ሰዓት የቴሌፎን መስመር (ሆትላይን) 202-849-3608 መልእክት መተው ይችላሉ።

7. የሸማቾች ህግ ሀብት ማእከል (ኮንሱመር ሎው ሪሶርስ ሰንተር) አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ጉዳዮች፣ እዳ መሰብሰብ፣ የኪራይ ቀብድ ማስመለስ (ሬንት ዲፖዚት ሪካቨሪ)፣ እና ሌሎች የሸማቾች ጉዳዮች በተመለከተ መረጃ ያቀርባል። እንደነ በባንክ ሂሳብዎ የተያያዘ ነገር (አታችመንት አፍ ባንክ አካውንት) የመሳሰሉትን የሸማቾች ጉዳዮች ቢኖርብዎ፣ እና አቤቱታና የክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ፣ የዲ.ሲ. ባር ፕሮ ቦኖ ማእከል - የሸማቾች ህግ ሀብት ማእከል (ኮንሱመር ሎው ሪሶርስ ሰንተር) ጊዜያዊ የቴሌፎን መስመር 202-780-2574 መደወል ይችላሉ።

እባክዎን የሚመለከታቸው የጸሀፊ (ክለርክ) ቢሮዎች በሚከተሉት የቴሌፎን ቁጥሮች በመደወል ወይም በክፍሉ ድረገጽ በቀኝ በኩል በሚገኝ ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) በሚል አዝራር (በተን) በመጫን ያግኙ።

*የፍትሐብሔር እርምጃ (ሲቪል ኤክሽን) ቅርንጫፍ፡*
202-879-1133
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/civil-matters/requesting-over-10k
ቅጂዎች ለመጠየቅ፡ CivilDocket@dcsc.gov

LIVE CHAT
Got a Question? Let us help

*የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ፡*
202-879-4879
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/civil-matters/landlord-tenant
ቅጂዎች ለመጠየቅ፡ LandlordandTenant@dcsc.gov

*አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች (ስሞል ክሊይምስ) ቅርንጫፍ፡*
202-879-1120
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/civil-matters/requesting-10k-or-less
ቅጂዎች ለመጠየቅ፡ SmallClaimsDocket@dcsc.gov

**የወንጀል ሰለባዎች ካሳ ፕሮግራም**

ሁሉም ከወንጀል ሰለባዎች ካሳ ፈንድ ለማግኘት የሚደረጉ ማመልከቻዎች በሰራተኞች በርቀት ሂደት እየተደረገላቸው ይገኛል። አዳዲስ ማመልከቻዎች ወደ CVCPapplications@DCSC.gov በኢሜይል መላክ ይችላሉ። ከማመልካቻው ጋር ወንጀል መፈጸሙ የሚያሳይ ሰነድ ያስረክቡ።

የወንጀል ሰለባዎች ካሳ ማመልከቻ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ይገኛል https://www.dccourts.gov/sites/default/files/CVCPApplicationMarch2020.pdf።

ማመልከቻው በኦንላይን ማጠናቀቅ የማይችሉ ከሆነ አዲስ እና ነባር የይገባኛል ጥያቄዎች በተመለከተ እርዳታ ለማግኘት ቢሮውን በቴሌፎን ቁጥር 202-879-4216 ወይም በኢሜይል CVCPOffice@dcsc.gov ማግኘት ይችላሉ።

እባክዎን ሁሉም ይግባኞች ወደ CVCPappeals@DCSC.gov ያስረክቡ።

**የወንጀል ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን)**

የፍርድ ቤት ጉዳዮች ዝርዝር (ኮርት ዳኬት) እና አንዳንድ ሰነዶች፣ እንዲሁም ደግሞ የመቀጮ እና ማካካሻ (ፋይንስ ኤንድ ረስቲትዩሽን) ክፍያዎች በምናብ (ኦንላይን) በhttps://eaccess.dccourts.gov/eaccess መደረግ ይችላሉ። እባክዎን የገንዘብ ዋስ (ቦንድ) ክፍያዎችን በጥሬ ገንዘብ መክፈል በተመለከተ ጥያቄዎች ቢኖርብዎ 202-879-1840 ይደውሉ።

የተረጋገጡ (ሰርቲፋይድ የሆኑ) ቅጂዎች ለማግኘት የሚደረጉ ጥያቄዎች በኢሜይል በCriminalMotionSealTeam@dcsc.gov ወይም በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1362 መደረግ ይችላሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ወይም የሰነዶች ቅጂ ለመጠየቅ እባክዎን የወንጀል ክፍል ጸሀፊ (ክለርክ) ቢሮ በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1373 ወይም በኢሜይል CriminalCaseManagement@dcsc.gov ያግኙ።

**የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)**

በድንገተኛ አደጋ ላይ ካሉ 911 መደወል ይኖርብዎታል። የጊዝያዊ መከላከያ ትእዛዝ (ቲ.ፒ.ኦ.) ወይም የፍትሐብሔር መከላከያ ትእዛዝ (ሲ.ፒ.ኦ.) በሚከተሉት ሶስት መንገዶች ፋይል ማድረግ ይችላሉ፡

1. ዲ.ሲ. ሴፍ ክሪቲካል ሪስፖንስ ቲም (ወሳኝ ምላሽ ሰጪ ቡድን) በ(800) 407- 5048 በመደወል፣
2. በwww.probono.net/dccourts በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ፣ ወይም
3. ወደ domesticviolencemanagement@dcsc.gov ኢሜይል በማድረግ።

የአንድ አካል ብቻ (ኤክስ-ፓርተ) እና የመጨረሻ እጅግ በጣም አደገኛ መከላከያ ትእዛዝ (ፋይናል ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደር) ጨምሮ ሌሎች ፋይል የሚደረጉትን ለማስረከብ እባክዎን ፋይል የሚደረጉትን በኢመይል ወደ domesticviolencemanagement@dcsc.gov ይላኩ። በሲ.ፒ.ኦ. ጉዳይ አካላት ስምምነት ላይ ከደረሱ የተስማሙበት የሲ.ፒ.ኦ. ስምምነት ወደ DVDhearings@dcsc.gov ኢመይል ማድረግ ይችላሉ።

ፋይል ሊደረጉ የሚችሉ (ፋይላብል) ቅጾች በዲ.ሲ. ፍርድ ቤት ድረገጽ http://www.dccourts.gov/services/forms?title=&combine ይገኛሉ።

ክፍሉ (ዲቪዥኑ)በኖቨምበር 9፣ 2020 የፍትሐብሔር መከላከያ ትእዛዝ ጉዳዮች በርቀት መስማት ጀምሯል። አካላት ቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም መሳተፍ ይኖርባቸዋል፣ ወደ ፍርድ ቤት ህንጻ በአካል መምጣት የለባቸውም።

የሰነዶች ቅጂዎች ለመጠየቅና የፍርድ ቤት ቀጠሮዎ፣ የርቀት ችሎት እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ፣ እና ማናቸውም ሌሎች የሚያሳስቡ ሁኔታዎች በተመለከተ ጥያቄዎች ቢኖርብዎ፣ እባክዎን ቢሮውን በ202-879-0157 ያግኙ ወይም የዲ.ሲ. ፍርድ ቤት ድረገጽን https://www.dccourts.gov/superior-court/domestic-violence-division ይጎብኙ።

### የቤተሰብ ፍርድ ቤት (ፋሚሊ ኮርት)

የቤተሰብ ፍርድ ቤት በኢፋይሊንግ (eFiling) በኩል የተላኩ ሰነዶች ሂደት ማድረጉ ይቀጥላል። አስቸኳይ አቤቱታዎች ለግምገማ ወደ ተመደበው ዳኛ ይላካሉ፣ ሁሉም ችሎቶች በርቀት ይካሄዳሉ። እባክዎን ሁሉም አስቸኳይ ጉዳዮች፣ ከበአላት በስተቀር፣ ከሰኞ እስከ አርብ ባሉ ቀናት ከ4፡00 ፒ.ኤም. በፊት ፋይል መደረግ እንደሚኖርባቸው ይገንዘቡ።

ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በhttps://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ የባለአደራነት (ካስተዲ)፣ ፍቺ እና/ወይም የልጅ ቀለብ ማመልከቻዎች በማጠናቀቅና ፋይል በማድረግ ዘንድ እርዳታ የሚፈልጉ ተከራካሪዎች የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከልን (ፋሚሊ ኮርት ሰልፍ ሄልፕ ሰንተር) በ202-879-0096 ያግኙ።

እባክዎን ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ወይም የሰነዶች ቅጂዎች ቢፈልጉ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የጥሪ ማእከል (ፋሚሊ ኮርት ኮል ሰንተር) በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1212 ያግኙ ወይም ወደ FamilyCourtCertifiedCopies@dcsc.gov ኢመይል ያድርጉ።

*የጋብቻ ቢሮ*

የጋብቻ ቢሮ የጋብቻ ፈቃዶች (መርየጅ ላይሰንስስ) ማመልከቻዎች በርቀት ሂደት በማድረግ ይገኛል፣ ጋብቻም በቪድዮ ኮንፈረንስ እያካሄደ ይገኛል። ሁሉም አካላት - ሁለቱም ተጋቢ አካላትና ጋብቻውን የሚያካሂደው ሰው- ስነ ስርአቱ በሚደረግበት ጊዜ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በአካል ያሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

የማመልከቻ ሂደቱ ለመጀመር በ https://www.dccourts.gov/form/marriage-application የሚገኘው ምናባዊ (የኦንላይን) ማመልከቻው አጠናቅቀው ያስረክቡ። ማመልከቻው ለማጠናቀቅና ለማስረከብ ኮምፒውተር ወይም ሞባይል መሳሪያ (አይፓድ፣ ታብሌት ወይም ስማርትፎን) መጠቀም ይችላሉ። የማመልከቻው ሂደቱ ለመጨረስ የጋብቻ ቢሮ ተወካይ ያገኝዎታል።

በምናብ (ኦንላይን) ማመልከት የማይችሉ ከሆነ እርዳታ ለማግኘት የቤተሰብ ፍርድ ቤት የጥሪ ማእከል (ፋሚሊ ኮርት ኮል ሰንተር) በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1212 ያግኙ።

ለአስቸኳይ ሁኔታ (የጤና ኢንሹራንስ፣ የልጅ መወለድ፣ ኢሚግሬሽን፣ ወዘተ) የጋብቻ ፈቃድ (መርየጅ ላይሰንስ) ወይም የተረጋገጠ ቅጂ (ሰርቲፋይድ ኮፒ) ቢፈልጉ፣ እባክዎን ወደ emergencycertifiedcopies@dcsc.gov ኢመይል ይላኩ። የጋብቻ ምስክር ወረቀት የተረጋገጠ ቅጂ ቢፈልጉ (አስቸኳይ ያልሆነ)፣ እባክዎን ይህን ቅጽ ይሞሉ፡ https://www.dccourts.gov/webform/marriage_certified_copy/። በተጨማሪ እርዳታ ለማግኘት 202-879-1212 መደወል ይችላሉ።

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክኒያትና በቢሮ አሰራር ባስከተለው ከፍተኛ ለውጦች ምክኒያት ሂደት (ፕሮሰስ) ለማድረግ ተጨማሪ ጊዜ ሊያስፈልግ ስለሚችል መዘግየት ሊኖር ይችላል። ለትእግስትዎ አስቀድመን እናመሰግንዎታለን።

## የጁሮሮች ቢሮ (ጁሮርስ ኦፊስ)




ጁሮሮች በምናብ (ኦንላይን) በwww.dccourts.gov/jurorservices በኩል የጁሮሮች መጠይቅ ማጠናቀቅ፣ የጁሪ ግዴታ አገልግሎት ማስተላለፍ፣ እና ከጁሪ ግዴታ አገልግሎት እንዲተዉ መጠየቅ ይችላሉ። ጁሮሮች በተጨማሪ የተጠናቀቀ መጠይቃቸው ወይም የተጠናቀቀ መጠይቃቸው ምስልን ለjurorhelp@dcsc.gov በኢመይል መላክ ይችላሉ።

የጁሮር ቢሮ በቴሌፎን በ202-879-4604፣ በኢመይል በjurorhelp@dcsc.gov ወይም በድረገጹ https://www.dccourts.gov/jurors/about-your-jury-duty በቀኝ በኩል በሚገኘው ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) የሚለውን አዝራር (በተን) በመጫን፣ ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:30 ኤ.ኤም. - 5፡00 ፒ.ኤም. ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ ነው። ግራንድ ጁሮሮችም ጥያቄዎቻቸው ወደ grandjurorhelp@dcsc.gov ኢመይል ማድረግ ይችላሉ።

## የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን)

የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) በኢፋይሊንግ (eFiling) በኩል የተላኩ ሰነዶች ሂደት ማድረጉ ይቀጥላል። አስቸኳይ ጉዳዮች (21-ቀን እና ጊዜያዊ ሞግዚትነት) ለግምገማ ወደ ዳኛ ይላካሉ፣ ሁሉም ችሎቶች በርቀት ይካሄዳሉ። በተጨማሪ፣ ችሎት ለማያስፈልጋቸው አስቸኳይ-ላልሆኑ ጉዳዮች ዳኞች ውሳኔ ይሰጣሉ።

1. ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በhttps://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

2. የ21-ቀናት ጊዝያዊ የሞግዚት ማመልከቻ ፋይል ለማድረግ ሰነዱን ወደ ProbateEmergencyFilings@dcsc.gov ኢሜይል ያድርጉ።

3. አዲስ የ90-ቀናት የጤና እንክብካቤ ሞግዚት ወይም ማመልከቻ ለአጠቃላይ የፍርድ ቤት ሂደት ፋይል ማድረግ ቢፈልጉ ማመልከቻው ወደ probatefilings@dcsc.gov ኢመይል ያድርጉ። የመዝገብ ቁጥር ያለዎት ከሆነ ማመልከቻው በኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በኩል በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይኖርበታል።

4. አስቀድሞ መከፈል ያለባቸው ክፍያዎች እንዳይከፍሉ መጠየቅ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን በድረገጻችን በhttps://www.dccourts.gov/services/judge-in-chambers/in-forma-pauperis-fee-waiver የሚገኘውን የክፍያ ነጻ አድርጉልኝ ማመልከቻን ይሙሉ።

5. የአስቸኳይ ጉዳይ አቤቱታ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ፣ ለኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ አስቸኳይ ፋይል የቴሌፎን መስመር (ፕሮቤት ኢመርጀንሲ ፋይሊንግ ቴሌፎን ላይን) በ202-879-9436 ማግኘት ይችላሉ።

6. በተጨማሪ፣ አስቸኳይ-ላልሆኑ ጉዳዮች የሚያስፈልጉ ሰነዶች በፖስታ ወደ D.C. Superior Court Probate Division, 515 5th Street, N.W. Washington, DC 20001. Attention: Probate Clerk's Office መላክ ይችላሉ።

አስቸኳይ ለሆነ ጉዳይ አቤቱታ እንዴት ማድረግ እንዳለብዎት ልዩ መመሪያዎች ከፈለጉ እባክዎን የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) ድረገጽ https://www.dccourts.gov/services/probate-matters ይመልከቱ።

የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) ከቴሌፎን ቁጥሮቻቸው ባንዱ ቁጥር በመደወልና መልእክት በመተው፣ ኢሜይል በመላክ፣ ወይም በክፍሉ ድረገጽ በቀኝ በኩል በሚገኘው ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) የሚለውን አዝራር (በተን) በመጫን ማግኘት ይቻላል።




የኑዛዜን ወይም ውርስን ህጋዊነት ማረጋገጥ (ፕሮቤት) አጠቃላይ ጥያቄዎች
ቴሌፎን፡ 202-879-9460 or 202-879-9461
ኢመይል፡ Probateinquiries@dcsc.gov

ልዩ የሞግዚትነት (ስፐሲፊክ ጋርድያንሺፕ) ጥያቄዎች
ኢመይል፡ GuardianshipAssistanceProgram@dcsc.gov.
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/probate-matters
ቅጂዎች ለመጠየቅ፡ Probatefilings@dcsc.gov

**የግብር ክፍል (ታክስ ዲቪዥን)**
ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በhttps://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ማመልከቻዎቻቸው (ፕሊዲንግስ) ወይም የማመልከቻዎቻቸው (ፕሊዲንግስ) ምስል በኢመይል አድራሻ TaxDocket@dcsc.gov በመላክ ፋይል ማድረግያ ክፍያቸው ደግሞ በቼክ ወይም ማኒ ኦርደር ለD.C. Superior Court, Tax Division, 500 Indiana Ave., NW, Suite 4100, Washington, DC 20001 መላክ ይችላሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ለግብር ክፍል (ታክስ ዲቪዥን)በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1737 ወይም በኢመይል TaxDocket@dcsc.gov ያግኙ።

*በተጨማሪ፣ ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ለሱፐርየር ፍርድ ቤት ጸሀፊ (ክለርክ) በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1400 ማግኘት ይችላሉ።*